የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 66
ADDIS ABABA-24th June,2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፮/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የኢትዮ–ኩባ የንግድ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ገጽ ፳፪፻፳፪

## CONTENTS

Proclamation No. 346/2003
Ethio–Cuba Trade Agreement Ratification Proclamation ........................................ Page 2222

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፮/፲፱፻፺፭
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኩባ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የንግድ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኩባ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት ጥቅምት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በሀቫና የተፈረመ ስለሆነ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ ፤

በሕገ – መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮ – ኩባ የንግድ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፵፮/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO, 346/2003
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE TRADE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF CUBA

WHEREAS, the Agreement on trade between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of Cuba was signed in Havana on the 4th day of November, 2000.

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 24th day of June, 2003.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub–Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethio–Cuba Trade Agreement Ratification Proclamation No. 346/2003."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኩባ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ሃቫና ላይ የተፈረመው የንግድ ስምምነት ፀድቋል።

፫· ስለ አስፈጻሚ አካል ሥልጣን

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Ethio–Cuba trade Agreement signed in Havana on the 4th day of November, 2000 is hereby ratified

3. *Power of Executive Organ*

The Ministry of Trade and Industry is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 24th day of June, 2003.

*Done at Addis Ababa, this 24th day of June, 2003.*

*GIRMA WOLDE GIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE